ሳምንት 4

4ኛ ክፍል

# የመጓጓዣ ዓይነቶች

Leveled



Amharic

ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2009 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.

For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*

# የመጓጓዣ ዓይነቶች

4ኛ ክፍል | ሳምንት 4 | Leveled



## የመምህራን ማስታወሻ

ይህ መጽሀፍ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሰረት የንባብ ክሂልን ለማሳደግ እና ልጆች ጥሩ የተዘጋጀ ነው። ተማሪዎች ይህንን መጽሀፍ ተጠቅመው የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ የወላጆች ና የመምህሮች እገዛና ክትትል እጅግ በጣም ወሳኝ ነው። መምህሮች፣ በመጽሀፉ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን በተገቢ መንገድና በትክክል በማንበብና በማስነበብ ድርሻችሁን ልታበረክቱ ይገባል። የተከበራችሁ መምህራን እና ሌሎች አጋዥ አንባቢዎች፣ ይህንን መጽሀፍ ለተማሪዎች ከማንበባችሁ በፊት በግላችሁ አንብቡና ሀሳቡን በመረዳት በቂ ዝግጅት አድርጉ።

### ቅደመ ንባብ ጥቄዎች

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. ርዕሱ ስታነቡ ምንባቡ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ::
2. ስዕሉን አይታችሁ የምንባቡን ሃሳብ ምን ሊሆን እንደሚችል ተናገሩ::



## ምዕራፍ አንድ፡ የመምህር ክንዱ ትዝታ

መምህር ክንዱ የ4ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ መምህር ነው፡፡ የዛሬው ትምህርት ርዕስ ስለመጓጓዣ ነው፡፡ መጓጓዣ ሲባል ሁሌም የማይረሳው አንድ ቀን ያጋጠመው አደጋ ነው፡፡ ዕለቱ ከጓደኞቹ ጋር የፈረስ ውድድር ያደረገበት ቀን ነበር፡፡ ለውድድሩ አዲስ የተገዛ ያልተገራ ፈረሱን ይዞ ቀረበ፡፡

ጓደኞቹም “ይህ ፈረስ ያልተገራና እንግዳ በመሆኑ ይጥልሃልና በዚህ ፈረስ መወዳደር ይቅርብህ” አሉት፡፡ እሱ ግን ምክራቸውን ወደጎን በመተው የፈረሱን ፈጣንነት በማየት ብቻ በእንግዳው ፈረስ ተወዳደረ፡፡ ፈረሱ በመጀመሪያ ቀስ እያለ መጋለብ ጀመረና በአንድ ጊዜ ሽምጥ ጋለበ፡፡ ክንዱ በልጓሙ ለማቆም ቢሞክርም ያልተገራ በመሆኑ ማቆም አልቻለም፡፡ በመጨረሻም ሁለት የፊት እግሮቹን በማንሳት ወደላይ እየዘለለ በማይጠበቅ ፍጥነት በሀይል ሮጠ፡፡

መምህር ክንዱን ከትልቅ ድንጋይ ላይ አሽቀንጥሮ ስለጣለው ቀኝ እጁ ተሰበረ:: የህክምና ድጋፍ ቢደረግለትም ሊድን ስላልቻለ ቁስሉ አመርቅዞ ወደሌላ የሰውነቱ አካል እንዳይተላለፍ ሲባል ሀኪሞች እንዲቆረጥ ወሰኑ:: ከዚያን ዕለት ጀምሮ ጥንቃቄ በጎደለው በባህላዊ መጓጓዣ በመጠቀም አንድ እጁን ያጣበትን ቀን በማስታወስ ሌሎችን ያስተምርበታል::

ዛሬም ለተማሪዎቹ የአካል ጉዳተኛ የሆነበትን ምክንያት ለመንገርና እነሱን ለመምከር ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን እያሰበ ወደመማሪያ ክፍል ገባ:: ከዚያም ከተማሪዎቹ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፈ:: ቀጥሎም የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ የመጓጓዣን ምንነት እንዲነግሩት ጠየቀ:: ተማሪ ሙላቱ “መጓጓዣ ሰውንም ሆነ የተለያዩ እቃዎችን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚያገለግል ህይወት ያለውና ህይወት የሌለው ነገር ነው” አለ::

## ህይወት ያላቸውና ህይወት የሌላቸው የመጓጓዣ ዓይነቶች

መምህሩም “ህይወት ያላቸውን የመጓጓዣ አይነቶች የሚነገረኝ አለ?” በማለት ጠየቀ። ተማሪ ትብለጥ እጇን አወጣችና “ህይወት ያላቸው የመጓጓዣ አይነቶች እንደየአገሩ ሁኔታና የእንስሳት አይነቶች የተለያዩ ናቸው። በእኛ አካባቢ የተለመዱት የመጓጓዣ አይነቶች ፈረስ፣ አህያ፣ በቅሎና ግመል ይመስሉኛል” አለች። መምህር ክንዱም ትብለጥን አመስግኖ “ህይወት የሌላቸው የመጓጓዣ ዓይነቶችንስ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ?” አለ።

ተማሪ ዘምዘምም “ብዙ ህይወት የሌላቸው የመጓጓዣ አይነቶች አሉ። እኔ ከማውቃቸው አውሮፕላን፣ መርከብ፣ መኪና፣ ታንኳና ጀልባን መጥቀስ እችላለሁ” አለች። መምህሩ ተማሪዋን አመስግኖ ሌላ ጥያቄ ጠየቀ። “መጓጓዣዎች አገልግሎት ከሚሰጡበት ቦታ አንጻር በሶስት ይመደባሉ። ምን ምን ተብለው እንደሚመደቡ የሚነግረኝ አለ?” በማለት ጠየቀ።

ሃያት እጇን አውጥታ "አንደኛው የየብስ ወይም የመሬት ላይ መጓጓዣ ይባላል፤ ሁለተኛው የአየር ላይ መጓጓዣ የሚባል ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የባህር ላይ መጓጓዣ ይባላል" አለች:: አሁንም መምህር ክንዱ ተማሪዋን አመስግኖ "ከእያንዳንዱ የመጓጓዣ ዓይነትስ ሁለት ሁለት የሚነግረኝ/ የምትነግረኝ ማን ነው/ናት?" በማለት ጠየቀ:: ኢብራሂም እጁን አውጥቶ ሲፈቀድለት "ከየብስ መጓጓዣ፣ መርከብና ባቡር፣ ከአየር መጓጓዣ፣ ሂሊኮፕተርና ሚግ፣ ከውሃ ላይ መጓጓዣ ደግሞ ታንኳና ጀልባ" አለ::

መምህር ክንዱም "በጣም ጥሩ!" በማለት ተማሪውን አመስግኖ "ኢብራሂም የጠቀሳቸው በሙሉ ህይወት የሌላቸው የመጓጓዣ አይነቶች ናቸው:: ህይወት ያላቸው እንደፈረስ፣ አህያ፣ ግመልና በቅሎ የመሳሰሉት የመጓጓዣ አይነቶች በሙሉ የየብስ ላይ መጓጓዣዎች ናቸው" አለ::

ሀያት ለሁለተኛ ጊዜ እጇን አውጥታ ሲፈቀድላት “ኢብራሂም ከዘረዘራቸው የመጓጓዣ ዓይነቶች የማላውቃቸው አሉ:: ለምሳሌ ታንኳና ሚግን ስማቸው ሲጠራ እንኳን ሰምቼ አላውቅም” አለች:: ከሀያት ጎን የተቀመጠችው ተማሪ ትብለጥ “መምህር እኔ ግን አውቃቸዋለሁ ልንገራት::” አለች:: መምህር ክንዱም እንድትነግራት ፈቀዳላትና “ነገርግን ሁላችን እንድንሰማ ድምጽሽን ከፍ አድርገሽ ተናገሪ” አሏት:: “ታንኳ ከደንገል የሚሰራ የባህር ላይ ትንሽ መጓጓዣ ሲሆን ሚግ ደግሞ የጦር አውሮፕላን ነው” አለች::

መምህሩም “ትክክል ነሽ! አንዳንዶቹን የመጓጓዣ አይነቶች ሃያት እንዳለችው ስማቸውን እንኳን ሲጠራ ሰምተን አናውቅ ይሆናል:: አንዳንዶቹን ደግሞ በስዕል፣ በፎቶ፣ በቴሌቭዥን አይተናቸው ሊሆን ይችላል:: ግን ስማቸውን ላናውቅ እንችላለን:: በአካል ያየናቸውም በርካታ የመጓጓዣ ዓይነቶች ይኖራሉ” አሉ::

## የጉዞ መርሃግብር

በመቀጠልም መምህሩ “ህያት ብቻ ሳትሆን ሁላችሁም ብትሆኑ ሁሉንም የመጓጓዣ አይነቶች በአካል አይታችሁ ላታውቁ ትችላላችሁ:: ስለዚህም በአካባቢያችን የሚገኙትን አንዳንዶቹን የመጓጓዣ ዓይነቶች ካሉበት ድረስ ሄደን እናያቸዋለን:: የጉዞው ቀን የሚቀጥለው ቅዳሜ ስለሆነ እናንተ ወላጆቻችሁን አስፈቅዱ:: እኔ ባለፈው ዓመት የተማሪዎች የአንድ ቀን የጉዞ መርሃግብር እንደሚኖር አሳውቄ ገንዘብ አስፈቅጃለሁ” አለ::

ሁሉም በጣም ከመደሰታቸው የተነሳ የሚይዙትን የሚጨብጡትን አጡ:: ተማሪዎቹ ከደስታቸው ብዛት መደማመጥ ጠፍቶ ሁሉም ተናጋሪ በመሆናቸው የሚያሰሙት ድምጽ ወደጨኸት ተቀየረ:: መምህር ክንዱ እንደምንም ብሎ ዝም አሰኛቸውና ተሰናብቶ ከክፍል ለመወጣት ተዘጋጀ:: ተማሪዎቹም መምህሩ አስቀድሞ በመዘጋጀቱ አመስግነው ለቅደሜው ጉዟቸው ወላጆቻቸውን አስፈቅደው እንደሚመጡ ተስማሙ::



## ምዕራፍ ሁለት፡ የጉዞ ዝግጅት

ተማሪዎቹ ቀኑ አልደርስ ብሏቸው ሲቅበጠበጡ ሰነበቱ፡፡ መመህሩም መጓጓዣና ሌሎች ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሲያመቻች ሰነበተ፡፡ ቀኑ ሲደርስ ተማሪዎቹ ከተባለው ሰዓት ቀድመው ደረሱ፡፡ መምህሩም በቅደሚያ ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላ ሁሉም ተማሪዎች መገኘታቸውን አረጋገጠ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ በጉዞ ወቅት ሊያደርጉት የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ነገሮች በዝርዝር አስረዳቸው፡፡

ለምሳሌ፦ የማታውቁትን ነገር የመጠየቅና የምታውቁትን ደግሞ ለሌሎች የማስረዳት መብት አላችሁ፤ በቅርብ ተጠግታችሁ በእጃችሁ በመነካካትና በመዳሰስ የምታዩአቸው የመጓጓዣ አይነቶች አሉ፤ መንካትም ሆነ መዳሰስ የማትችሉበት አጋጣሚም አለ፡፡ እንደአህያና በቅሎ የመሳሰሉ እንስሳትን በተለይ የኋላ እግራቸውን መንካት አደጋ አለው፡፡ በተጨማሪም በመጓጓዣዎቹ መጠቀም የምትችሉት አስፈቅዳችሁ አደጋ የማያስከተል ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ሳታስፈቅዱ የምትነኩ ከሆነ እንደእኔ አካላችሁን ልታጡ ትችላላችሁ” በማለት አስጠነቀቃቸው፡፡

## ጉዞ ወደአየር መንገድ

መምህር ክንዱና ተማሪዎቹ ከትምህርትቤት በተመደበላቸው ገንዘብ በተከራዩት መኪና በቀጥታ ወደአየር መንገድ ሄዱ:: ከመግቢያው በር ላይ ሲደርሱ ጸጥታ አስከባሪዎች አስቆሟቸው:: መምህር ከንዱ ተማሪዎቹን ይዞ እንደሚመጣ አስቀድሞ አሰፈቅዶ ስለነበር መታወቂያውንና ከትምህርትቤት የተሰጠውን የትብብር ደብዳቤውን አሳየ:: ጸጥታ አስከባሪዎችም ልጆቹንና መኪናውን ፈትሸው እንዲገቡ ፈቀዱላቸው::

ከዚያም መምህር ክንዱ ወደእንግዶች ማረፊያና የጉዞ ፈቃድ ማረጋገጫ ቦታ በተለመደው መሰረት አሰፈቅዶ ተማሪዎቹን ይዞ ገባ:: የመንገደኞቹን ሁኔታ በስነስርዓት ቁጭ ብለው ሲመለከቱ ቆዩ::

መምህር ክንዱና ተማሪዎቹ ትንሽ እንደጠበቁ አውሮፕላኑ መጣ:: "የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር ET124 የበረራው ሰዓት ደርሷል" የሚል ጥሪ ከበረራ አስተናጋጆች ተሰማ:: በዚህ ጊዜ መንገደኞቹ ወደአውሮፕላኑ በሚያስገባው በር በሰልፍ መግባት ጀመሩ:: ተማሪዎቹ መምህር ክንዱ እንዳይንቀሳቀሱ በእጁ ምልክት አሳይቷቸው ስለነበር እንደተቀመጡ ዝም አሉ::

መንገደኞቹ ከውጡ በኋላ ተማሪዎቹ ስልፍ ይዘው እንዲወጡ ተፈቀደላቸው:: ነገርግን በርቀት እንዲመለከቱ እንጂ መቅረብ እንደማይችሉ መምህሩ ነግሯቸው ስለነበር አውሮፕላኑ እስኪንቀሳቀስ ድረስ ሁሉንም የአውሮፕላኑን አካላት ተመለከቱ:: አውሮፕላኑም ከመንቀሳቀሱ በፊት መወጣጫው መሰላል ተነስቶ በሩ ተዘጋ:: ከዚያም እንደመኪና በጎማዎች መንቀሳቀስ ጀመረ:: ትንሽ አንደሄደ ፍጥነቱን ጨምሮ በመሬት ከተጓዘ በኋላ መሬቱን ለቆ በሰማይ መብረር ቀጠለ:: ተማሪዎቹም ከመምህራቸው ጋር በመሆን አውሮፕላኑ ከአይናቸው እስኪሚሰወር ድረስ በአትኩሮት ሲመለከቱት ቆዩ:: ከዚያም የአየር መንገድ ሰራተኞችን አመስግነው በመሰናበት በመጡበት ሁኔታ ከግቢ ወጡ::

መምህራቸው “ምንም እንኳን አውሮፕላኑን በእጃችን መዳሰስ ባንችልም በዓይናችን ሁሉንም የአውሮፕላኑን ክፍሎችና እንቅስቃሴውን ለመመልከት ችለናል” አለ:: ተማሪዎቹም አውሮፕላን እንዲያዩ ስለአደረጋቸው መምህራቸውን አመስግነው፣ የሚቀጥለው ጉዟቸው የት እንደሚሆን መምህራቸውን ጠየቁ::

## ጉዞ ወደጎርጎራ

መምህር ክንዱም "ቀጣዩ ጉዟችን የሚሆነው ወደጎርጎራ ነው፤ እግረ መንገዳችን በመንገድ ላይ አንዳንድ መጓጓዣዎችን እናያለን" አለ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ወደመኪናቸው ገብተው ቦታ ቦታቸውን ያዙ፡፡ መምህር ክንዴም በመጨረሻ ገባና ተማሪዎቹ በትክክል መቀመጣቸውን ካረጋገጠ በኋላ ጉዟቸውን ወደጎርጎራ አቀኑ፡፡ ትንሽ እንደተጓዙ በመንገድ ላይ አህያ የጫነ አንድ ሰው ተመለከቱ፡፡ መምህሩም ሾፌሩን አህያ የጫነው ሰው አጠገብ ሲደርሱ መኪናውን እንዲያቆም ነገረው፡፡

ከዚያም መምህሩ ተማሪዎቹን እንዲወርዱ አደረገና የአህያውን የኋላ እግር ሳይነኩ እንዲመለከቱ ነገራቸው፡፡ በፊት በኩል ግን እየነካኩ ሊመለከቱ እንደሚችሉም አስረዳቸው፡፡ በመቀጠል የአህያውን ባለቤት አስፈቀደና ልጆቹ እንዲመለከቱ አደረገ፡፡ ተማሪዎቹ በአህያው በፊት በኩል በመሆን አይኑን ጆሮውን አፍንጫውን እግሮቹንና ጭነቱን ሳይቀር ተመለከቱ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ አህያው ምን ያህል ጭነት እንደሚሸከም፣ ምን እንክብከቤ እንደሚያደርግለትና ሌላም የመጓጓዣ አይነት እንዳለው ባለቤቱን ጠየቁት፡፡

ባለቤቱም ደስ እያለው ሁሉንም ጥያቄዎች አንድባንድ መለሰ:: ልጆቹም አመስግነው ወደመኪናቸው ገቡ::

በየመንገዱ የሚያገኟቸውን መጓጓዣዎች በሙሉ እየተመለከቱና እያደነቁ ተጓዙ:: ጎርጎራ ሊደርሱ ትንሽ ሲቀራቸው አንድ ሰው በቅሎ ላይ ተቀምጦ ከሩቅ ሲመጣ ተመለከቱ:: አሁንም መምህር ክንዱ በቅሎም እንደአህያ ተመሳሳይ ባህርይ ስላለው የኋላ እግሩን ከነከሉት ሊመታቸው ስለሚችል በፊት በኩል እንዲመለከቱ አስጠነቀቃቸው:: ከዚያም ሰውዬው ጋ ሲደርሱ መኪናቸውን አቆሙና ወረዱ:: ከዚያም መምህራቸው እንደነገራቸው በቅሎውን ተመለከቱና ሰውዬውን ለአህያዋ ባለቤት የጠየቁትን ጥያቄዎች በሙሉ ጠየቁትና ተገቢ መልሶችን አገኙ::

ከዚያም ወደመኪናቸው ገብተው ትንሽ ከተጓዙ በኋላ ጎርጎራ ከተማ ደረሱ:: መምህር ክንዱም ሾፌሩ መኪናውን ወደግራ አጥፎና ቁልቁል ወደወደቡ እንዲወርድ አቅጣጫውን አሳየው:: ሾፌሩም የተጠቆመውን አቅጣጫ ተከትሎ ወደወደቡ ወረደ:: ልጆቹም ወደቡ ጥግ የተደረደሩትን ታንኳዎች፣ ጀልባዎችና ጣናነሽን ሲመለከቱ ቶሎ ለመውረድ ፈለጉ::



## ምዕራፍ ሶስት፡ የውሃ ላይ ጉዞ

መምህር ክንዱ ተማሪዎቹ ለመውረድ ሲገፋፉ ተመልክቶ “ልጆች! ከመኪና ስትወጡም ሆነ ስትወርዱ ተራ በተራ መሆን እንዳለበት ነግሬያችሁ ነበር። ረሳችሁት እንዴ! ተው እንጂ! ቀስ በሉ!” አለ ቆጣ ብሎ። ልጆቹ በተባሉት መሰረት ተራ በተራ ከመኪናው ወረዱና መንገዱን በመከተል ወደወደቡ ተጠጉ። ትናንሽ ጀልባዎችና ታንኳዎች ወዳሉበት አካባቢ በፍጥነት ሮጠው ደረሱ። ተማሪዎቹ የውሃማ አካላት መጓጓዣ ባለቤቶችን መምህር ክንዱ አስፈቀዳቸውና ጀልባዎቹንና ታንኳዎቹን መነካካት ጀመሩ።

የትኛው ጀልባ የትኛው ታንኳ እንደሆነ መለየት ስላልቻሉ ትብለጥን ጠየቁ። ትብለጥም “ይሄኛው ከደንገል የተሰራው ታንኳ ሲሆን ከቆርቆሮ የተሰራውን ይኼኛውን ግን አላውቀውም” አለች። ሁለቱንም በእጇ እየነካች። ከዚያም መምህራቸው “ይሸኛው ደግሞ ጀልባ ነው” አለ ከቆርቆሮ የተሰራውን እያሳየ። ቀጥሎም “ልጆች አሁን ከጀልባዎቹና ከታንኳዎቹ ላይ በመውጣት በደንብ እናያቸዋለን” አለ።

ልጆቹም በጀልባዎቹና በታንኳዎቹ ላይ ሆነው የሀይቅ ላይ ጉዞ እንደሚያደርጉ ሲሰሙ በደስታ ዘለሉ። ከዚያም መምህሩ “ጉዞው የሚደረገው በተራና በእርጋታ ነው። በመጀመሪያ አንዱ ጀልባ ስንት ሰው እንደሚይዝ፣ ምን ያህል ርቀት በሀይቁ ላይ እንደሚጓዝና ዋጋው ስንት እንደሆነ የጀልባዎቹን ባለቤት እጠይቃለሁ” አለ። የጀልባዎቹ ባለቤቶች (ካፒቴኖች) በዚያው አካባቢ ቆመው የሚሆነውን እየተመለከቱ ስለነበር መምህሩ እነሱን ለመጠየቅ ዞር ሲል በፍጥነት መጥተው ከፊቱ ቆሙ። “ጋሼዬ! የእኔን፣ ጋሼዬ! የእኔን፣ ሰፊ ነው! ምቾት አለው!...” እያሉ አዋከቡት።

መምህር ክንዱም ፈገግ ብሎ በእርጋታ “አይዟችሁ! ሁሉንም ጀልባዎች እንፈልጋቸዋለን፤ እንደምታዩን ቁጥራችን ብዙ ነው። እናንተ ደግሞ አምስት ናችሁ፤ ስለዚህ አንዳችሁ ባአንድ ጊዜ ስንት ልጆች እንደምትይዙ፣ ዋጋችሁንና ስንት ኪሎ ሜትር እንደምትጓዙ ንገሩኝ” አለ።

ከዚያም ከባለጀልባዎቹ አንዱ “ጉዞው ስንት ኪሎ ሜትር ነው ለተባለው በአቅጣጫ ነው እንጂ በልኬታ አይደለም፤ ቀጥታ ወደፊት እንሄዳለን፤ ከዚያም ወደግራና ወደቀኝ እያልን ተጓዦቹ የሚፈልጉትን ጊዜ ያህል ልናቆያቸው እንችላለን:: የመጓጓዣ ዋጋም ቢሆን የሚወሰነው በውሃው ላይ በምናደርገው የቆይታ ጊዜ ነው:: በአንድ ጀልባ ውስጥ ስንት ልጆች ይሁኑ? ለሚለው ደግሞ ልጆቹ ህፃናት ስለሆኑና ክብደታቸውም ቀላል ስለሚሆን የጀልባው ቦታ የሚችለውን ያህል ይቀመጣሉ” አለ::

መምህር ክንዱም በተባለው ሃሳብ ተስማምቶ ልጆቹ ተራ በተራ ከህይቁ አጠገብ ተሰልፈው ከቆሙት ጀልባዎች እንዲገቡ አደረገ:: ከዚያም በውሃው ላይ ሲጓዙ አላስፈላጊ እንቅስቃሴ ማድረግም ሆነ መገፋፋት ተገቢ አለመሆኑን ገለጸላቸው:: በተጨማሪም “ሁላችሁም በተቀመጣችሁበት ቦታ ሆናችሁ የምትፈልጉትን መመልከትና ያልገባችሁን ነገር ካፕቴኑን መጠየቅ ትችላላችሁ” በማለት እንዲሄዱ ፈቀደላቸው::

መምህር ክንዱ ወደቡ ጥግ ቦታ ፈልጎ ተቀመጠና የጀልባዎቹን እንቅስቃሴ መመልከት ጀመረ:: የጀልባዎቹን አቅጣጫ ተከትሎ አይኖቹን ከወዲያ ወዲህ እያንከራተተ በሃሳቡ ግን ወደኋላ ተጉዞ የልጅነት ሕይወቱን አስታወሰ:: በልጅነቱ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን የሰፈራቸውን ሀይቅ እንደፈለጉ ሲጫወቱበት ይውሉ ነበር:: ሲፈልጉ ሲዋኙ፣ ሲፈልጉ ደግሞ በሰሩት ታንኳ ሀይቁን እየቀዘፉ ከወዲያ ወደህ ሲንሸራሸሩ፣ ሲሰለቻቸው ደግሞ አሳ በማስገር ከሀይቁ ዳር ጠብሰው ሲበሉ ይውሉ እንደነበር በዓይነ ህሊናው ሲቃኝ ቆዬ::

ድንገት ከሀሳቡ ሲነቃ ጀልባዎቹ በረድፍ በእኩል ፍጥነት ፊታቸውን ወደወደቡ አዙረው ሲመጡ ተመለከተ:: ሃሳቡን ለማሰባሰብ እየሞከረ ለአፍታም ቢሆን ልጆቹን ከሃሳቡ በማውጣቱ እያፈረ በሰላም በመመለሳቸው በመደሰት ተነስቶ ቆመ:: የጀልባዎቹ ካፕቴኖች ሁሉም በአንዴ በተመሳሳይ አቅጣጫ አንዴ ወደምስራቅ፣ አንዴ ወደምዕራብ እየተመላለሱ ከወደቡ ጥግ ደረሱ:: ካፕቴኖቹ የጀልባዎቹን ሞተር በማጥፋት በሩን ሲከፍቱ ልጆቹ ተራ በተራ እየወጡ ወደመምህራቸው በመሮጥ አንገቱ ላይ ተጠመጠሙ::

መምህር ክንዱም አንገቱ ላይ የተጠመጠሙትን ልጆች ራሳቸውን እየዳበሰና እየሳመ፤አንገቱን አስለቀቀ። ከዚያም ካፕቴኖቹ የጠየቁትን ገንዘብ በመክፈል ከልጆቹ መሃል በመቆም በደስታ ተሞልተው የተሰማቸውን ለመናገር የቸኮሉትን ልጆች ተመለከታቸው። “ልጆች! አሁን ወደወደቡ ክበብ እንሂድ በትእዛዝ የተዘጋጀልንን ምሳ እየበላን ሁሉንም ትነግሩኛላችሁ” አላቸውና ወደዚያው ተጓዙ።

ክበቡ እንደደረሱም በአንድ አስተናጋጅ አማካይነት ከተዘጋጀላቸው ቦታ ተቀምጠው እየተጫዋወቱ ምሳቸውን በሉ። በመጨረሻም መምህር ክንዱ “እንግዲህ ተማሪዎች ከጧት ጀምሮ የአየር፣ የየብስና የባህር ላይ ዘመናዊና ባህላዊ መጓጓዣዎችን አይተናል። አሁን ሳይመሽብን ወደቤታችን እንመለስ አለና ሂሳብ ከፍሎ ልጆቹን አስከትሎ ከክበቡ በመውጣት ወደጎንደር ተመለሱ።

**ስሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ ስጡ።**

1. መፅሃፉ ስለምን እንደሚገልፅ የገመታችሁት ግምት ትክክል ነበር?
2. ህይወት ያላቸውን የመጓጓዣ አይነቶችን ዘርዝሩ።
3. ህይወት የሌላቸውን የመጓጓዣ ዓይነቶችን ዘርዝሩ።
4. በአካባቢያችሁ ምን ምን የመጓጓዣ ዐይነቶች አሉ?
5. እናንተ የትኛውን የመጓጓዣ ዓይነት ትወዳላችሁ? ለምን?

